# JLIB-የተማሪ ቀድሞ ከትምህርት ቤት መውጣት ማስታወቂያዎች

ተማሪዎች በርዕሰ መምህሩ ስልጣን ብቻ በማናቸውም ጊዜ ቀድመው ከትምህርት ቤት ለመውጣት ይችላሉ። ተማሪው ቀድሞ ለመውጣቱ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወይም ሌላ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ጥያቄው ለመቅረቡ እርግጠኛ እስከሆነ ድረስ፣ ርዕሰ መምህሩ ለተማሪው ያለጊዜው መውጣት የስልክ ሆነ የጽሑፍ ማስታወቂያ የመላክ ግዴታ የለበትም። ተማሪው ቀድሞ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ፈቃድ ስለመጠየቁ ጥርጣሬ ካለ፣ ርዕሰ መምህሩ ጥያቄውን ስልክ በመደወል ያጣራል። በማናቸውም ሁኔታዎች፣ ርዕሰ መምህሩ በስልክ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ትክክለኛነት ያጣራል።

ተማሪው አብሮት በጊዜ ከትምህርት ቤት የሚወጣው ሰው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወይም በወላጅ/አሳዳጊ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው መሆኑ እስካልታወቀ ድረስ ተማሪው በጊዜ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ሊፈቀድለት አይችልም።

የተማሪው ወላጆች ወላጅነት መብት ችግር ውስጥ በሚኖርበት ሁኔታዎች ውስጥ፣ ርዕሰ መምህሩ እንዲያሳድግ በኮሎራዶ ፍርድ ቤት በቀጥታ ስልጣን የተሰጠውን እና በትምህርት ቤቱ የተመዘገበ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ስለ ሁኔታው የተሰጠውን መመሪያ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል። በትምህርት ክፍለ ዘመኑ የማሳደግ ኃላፊነት ለውጥ ሲኖር ለቦታው ተገቢነት ካለው ከኮሎራዶ ፍርድቤት የፍርድ ትዕዛዝ ቅጂ መቅረብ አለበት።

ለከፍተኛ ድንገተኛ አደጋ ለዚህም ከርዕሰ መምህሩ ልዩ ፈቃድ ሲሰጥ ካልሆነ በቀር ማንም ተማሪ ከትምህርት ቤቱ ተወስዶ ከትምህርት ቤቱ ቅጽረ ግቢ ውጭ ወዳለ ወደ ሌላ ቦታ እንደ መልዕክተኛ ሊላክ አይችልም።

እንዲጣጣም ተደርጎ የተዘጋጀው ማርች 1፣ 1957 እና ኤፕሪል 15፣ 1971
ከበእጅ የሚሰራ ማጣጣም ሥራ ጋር እንዲጣጣም ተብሎ የተከለሰ

ተዛማጅ ማጣቀሻ፥ JIH፣ ምርመራዎች፣ ፍተሻዎች እና መታሰሮች
JLF፣ የልጅ የወሲብ ጥቃትን ሪፖርት ማድረግ/ የልጅ ጥበቃ